"ኢትዮጵያ ባዮሜትሪክስ ማህበር"

መተዳደሪያ ደንብ



ጥቅምት 25/2002 ዓ.ም

"ኢትዮጵያ ባዮሜትሪክስ ማህበር"

መተዳደሪያ ደንብ

መግቢያ

ባዮሜትሪክስበግብርና ላይ የሚሠሩ ጥትና ምርምሮች በዋና መሣሪያነትና ችግር ፈቺነት የሚያገለግል ከስታስቲክስ ክፍል አንዱ አካል ነው፡፡ በመሆኑም ባዮሜትሪሻንስ፣ ሜዲካል ስታስቲሻንስ፣ ኢፒዲሞሎጂስቶችና የተለያዩ የጤና አጠባበቅ ኤክስፐርቶች በሀገሪቱ ውስጥ ሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች፣ የግብርና ምርምር ተቋማት፣ በጤና ጥበቃ፣በግብርና ሚኒስቴርና ተዛማጅነት ያላቸው ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህንኑ የባዮሜትሪክስ ሞያ ለማሳደግና ባለሞያዎች ያላቸውን እውቀት በሚገባ በተግባር ላይ እንዲያውሉ የልማድ ልውውጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኢትዮጵያ ባዮሜትሪክስ ማህበር በ1993 ዓ.ም በባለሞያዎቹ ጥያቄ መሠረት እስከዛሬ ድረስ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ወቅት እንደገና ለመመዝገብ ይህን ተሻሽሎ የተዘጋጀውን የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡

አንቀጽ 1: መቋቋም

"ኢትዮጵያ ባዮሜትሪክስ ማህበር" የተባለ ማኅበር 1 ቀን ጳጉሜ ወር በ1993 ዓ.ም. ተቋቁሟል፡፡

አንቀጽ 2: ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ማኅበር "ኢትዮጵያ ባዮሜትሪክስ ማህበር" በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ "ማኅበር" ተብሎ ይጠቀሳል፡፡

አንቀጽ 3: ዓላማ

የማህበሩ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ) ሒሳብ ነክ ጉዳዮችና ባዮሜትሪክስ በባውሎዲካል ሳይንስ ላይ ጥቅም ለማዋል የመገናኛ መድረክ ለመፍጠር፣

ሰ) በግብርና፣ በጤናና በእንስሳት ሕክምና ላይ ጥናትና ምርምር የሚያከናውኑ ተመራማሪዎችን ባዮሜትሪክስ በምርምር ላይ ያለውን ጥቅም ማሳወቅ፣

ሐ) የባዮሜትሪክስ እውቀት በመጠቀም በሠነ-ተዋልዶ፣ በጤና እና በግብርና ላይ ውጤታማ አሰራሮችን በመፍጠር የአባላቱን ግንዘቤ ማስፋት፣

መ) የመገናኛ መድረክ (Network) ከባዮሜትሪክስ፣ ከኢፒዲሞሎጂስት፣ ከግብርናና፣ ከጤና አጠባበቅ ባለሞያዎች (Experts) በሀገር አቀፊና በዓለም አቀፍ ደረጃ በመፍጠር ባዮሜትሪክስን ማራመድና ማሳወቅ፣

አንቀጽ 4፡ የበጀት ዓመት

የማህበሩ የበጀት ዓመት እ.አ.አ. ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል።

አንቀጽ 5፡ ትርጉም

1. "ማኅበር" ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመው "ኢትዮጵያ ባዮሜትሪክስ ማህበር" ማኅበር ነው።
2. "ኤጀንሲ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 621/2001 የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ነው።
3. "ጠቅላላ ጉባኤ" ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማህበሩ የበላይ አካል ነው።

አንቀጽ 6፡ መደበኛ አባላት

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላው ጉባዔ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል።
2. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ/የምታሟላ ማንኛውም/ዋም ኢትዮጵያዊ/ት ሰው መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ትችላለች።

ሀ. በማህበሩ አላማና ግብ የሚያምን/የምታምን፤

ለ. እድሜው/ዋ ከ15 ዓመት በላይ የሆነ/ች፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
The Charities and Societies Agency

ሐ. የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ የሥነ-ምግባር ደንቦችን የሚቀበል/የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ/የምታደርግ፣

መ. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል/የምትችል

ሠ. በህግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ/ያልተገፈፈች።

አንቀጽ 7፡ የክብር አባላት

1. የማህበሩ አባል ያልሆኑና የማህበሩን አላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፤ የማህበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በማህበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ።

2. የክብር አባላት በማህበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም።

3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም።

አንቀጽ 8፡ የአባላት መብት

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው።

2. የማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው።

3. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል፦

ሀ. ስማህበሩ ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅመው ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣

ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለ ማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣

ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለ ማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት፣ እና

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
The Charities and Societies Agency

መ. አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በስራ አስፈጻሚ ቦርድ የመሰማት መብት አለው።

አንቀጽ 9፡ የአባላት ግዴታ

1. ማንኛውም/ዋም አባል የአባልነት መዋጮን በወቅቱ የመክፈል ፣
2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ኗ በፊት የሚፈለግበትን/የሚፈለግባትን ዕዳ የመክፈል ፣
3. ማንኛውም አባል የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሣኔዎችን የማክበር ፣
4. ማንኛውም አባል የማህበሩን አሳማና የገባቸውን/የገባችውን ግዴታዎች የማክበር፣ የማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ፣
5. በማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት ::

አንቀጽ 10፡ የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. የማህበሩ መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች የሚደረጉበት ጊዜና መጠን በጠቅላላ ጉባኤው ይወሰናል።
2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል ሰው በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል/ይጣልባታል።
3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሳ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን/የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ/ች አባል ላይ እዳውን/እዳዋን እስኪከፍል/እስክትከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ የመስጠት ወይም ማንኛውንም ሌላ መብት ሊያነሳ ይችላል::

አንቀጽ 11፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

አንድ የማህበሩ አባል አባልነቱ/ኗ የሚቋረጠው፦

1. ሲሞት/ስትሞት፣
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም በሌላ አኳኋን ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Charities and Societies Agency

3. የማህበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣

4. ለማህበሩ ዓላማ መሣካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተግባር ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸው በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣

5. መዋጮውን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ በጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፣

6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታው/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ/ስትወገድ፣

7. ከማህበሩ አባልነት በራሱ/ሷ ፈቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ/ስትጠይቅ ይሆናል፣

አንቀጽ 12፡ የማኅበሩ አደረጃጀት

1. የማሕበሩ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የስራ አመራር ቦርድ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ኦዲተር፣ ሂሳብ ሹም፣ ገንዘብ ያዥና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖረዋል።

2. የማህበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው :-





3. የቦርድ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ወይም ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሊሰራ አይችልም።

አንቀጽ 13፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፣

   ለ. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣

   ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማህበሩን አዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ክፍያውን ይወስናል፣

   መ. የቦርድ አባላትን፣ የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሾማል ይሽራል፣

   ሠ. የማህበሩን ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣

   ረ. የማህበሩ መፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣

   ሰ. የማህበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የአዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣

   ሸ. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣

   ቀ. በማህበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣

   በ. የማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

   ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

   ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣

   ኀ. የማህበሩ ሂሳብ በውጭ አዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣

   ነ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣

   ኘ. ማህበሩ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሠጣል።

   አ. በማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ የማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል።

2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሠ)፣ (በ)፣ (ቸ) እና (ኀ) መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማህበሩ ኦዲተር ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agency for Charities and Societies

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።

አንቀጽ 14: የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል።
2. ማንኛውም የማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው።
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ይኖርባታል።
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል።
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃሣብ ያለው/ያላት የማህበር አባል የልዩነት ሀሣቡን/ቧን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች።
6. ማንኛውም መደበኛ የማህበሩ አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች።

አንቀጽ 15: የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት

ጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

1. የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ፣

   ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች እንዲሁም ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

   ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣

   ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣

   መ. ጉባኤው ያጸደቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፣ የሥራና የአዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Charities and Societies Agency

እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣

ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሐፊው/ዋ በአጅንዳነት ያስይዛል/ታስይዛለች፣

2. ምክትል ሰብሳቢ

ሀ. ሰበሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፣

ለ. በሰብሳቢው/ዋ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ሰራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣

3. ፀሐፊ

ሀ. ከሰብሳቢው/ዋ ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉበኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

አንቀጽ 16: የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሊቀመንበሩ በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ እንደሆን ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከሆነ ኤጀንሲው የጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የሚሆን/የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል።

4. የማህበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በቦርዱ ስብሳቢ ወይም ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል።

5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ቀኑን፣ እንዲያውቁት ይደረጋል።

6. የማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

7. በዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች።

8. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳነት እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሐፊ/ሊቀመንበር/ፕሬዘዳንት/የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ/ በጽሁፍ ይሆነኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል።

አንቀጽ 17: የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ማህበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣

2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣

3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣

4. ጠቅላላ ጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እንደአስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣

5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቅማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ሰ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ ቢያንስ ለአንድ የምርጫ ዘመን (4 ዓመት) ማረፍ ይኖርባቸዋል።

6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣

7. የማህበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆችን የተከተለ መሆን አለበት።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
The Charities and Societies Agency

8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም::ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣

9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣

10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱ ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣

11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ላይ ቀርበው ያልጸደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

አንቀጽ 18፡ የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የሥራ አመራር ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የማኅበሩን ሥራ አስኪያጅ ይሾማል፣ ይሽራል፣

2. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡ ውሣኔዎችንና የሚወጡ እቅዶችን በሥራ አስኪያጁ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣

3. የማኅበሩን ፖሊሲ ለማውጣት ወይም ለማሻሻል የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ አካል የሚያቀርባቸውን ሀሳቦች ተቀብሎና አስፈላጊም ሲሆን የራሱን አስተያየት ጨምሮ ውሣኔ እንዲሰጠባቸው ለጉባኤው ያቀርባል፣

4. በገንዘብ ወይም በማቴሪያል ለማኅበሩ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚሆኑ ገቢዎች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣ ድጋፍ የሚገኝበትንም መንገድ ይቀይሳል፣

5. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ አካባቢዎች እንደአስፈላጊነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስወስናል፣

6. የማኅበሩ የስራ አስፈፃሚ አካላት የሚቀርቡ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርቶችን መርምሮ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

7. የማኅበሩ ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣



8. በማኅበሩ የአሞር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት ላይ በመምከር ለጠቅላላው ጉባኤ ለውሣኔ ያቀርባል፣
9. የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣
10. የቦርዱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ይወጣል፣
11. አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚጠራበት ምክንያት ሲያጋጥም ጥሪ እንዲደረግ ይወስናል።

አንቀጽ 19፡ የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

1. የሥራ አመራር ቦርድ ከ5-7 አባላት ይኖሩታል፣
2. ቦርዱ ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ይመርጣል፣
3. የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ድምጽ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ ሆኖ ይሰራል፣
4. ሰብሳቢው/ዋ፡-
   ሀ. የቦርዱን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፣
   ለ. ቦርዱ በስብሰባ ያሳለፋቸውን ውሣኔዎች ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባል፣
   ሐ. ቦርዱ የሚያወጣቸውን የማኅበሩን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ለጠቅላላው ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል፣
   መ. ለጠቅላላ ጉባኤውና ለቦርዱ ከተሰጠው ሥልጣን አንፃር ተጠሪነቱ ለጉባኤውና ለቦርዱ ይሆናል፣
   ሠ. ጠቅላላው ጉባኤና ቦርዱ የሚያሳልፏቸው ውሣኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፣
   ረ. የማኅበሩን ማኔጅመንት የሥራ አፈፃፀም በቅርብ ይከታተላል፣
   ሰ. ጉባኤው ያፀደቀውን የሥራ አፈፃፀምና የአዲት ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲልክ ለሥራ አስኪያጁ ትዕዛዝ ያስተላልፋል፣
   ሸ. ከአዲት ሪፖርት ውጭ ደሉትን ዓመታዊ ሪፖርቶች በጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የበጎ አድራጎት እና ማኅበራት ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia The Charities and Societies Agency

5. ምክትል ሰብሳቢ፦

ሀ. ሰብሳቢው በሌለ ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ ይሠራል፣

ለ. በሰብሳቢው ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጠውን ተጨማሪ ሥራ ያከናውናል

6. ፀሐፊ፦

ሀ. ተጠሪነቱ ለቦርዱ ነው፣

ለ. የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳዎች ከሰብሳቢው ጋር በመነጋገር ያዘጋጃል፣

ሐ. የቦርዱን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣

መ. የቦርዱ ጽ/ቤት መዛግብትና ሀብት ይጠብቃል።

አንቀጽ 20፦ የሥራ አመራር ቦርድ የስብሰባ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን

1. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በቦርድ ሰብሳቢ ወይም በማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሊጠራ ይችላል፣
3. ከቦርዱ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል። በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምጽ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሣብ ይፀናል፣
5. የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመት ይሆናል፤ ሆኖም አንድ የቦርድ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፣
6. የቦርድ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ሆኖም ለማኅበሩ ስራ ሲሚወጡት ወጪዎች ማካካሻ ይከፈላል።

አንቀጽ 21፦ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agency for Charities and Societies

1. በማናቸውም አካል ዘንድ ማኅበሩን ይወክላል፣ የማኅበሩን ሥራ በተመለከተ ማናቸውም ጉዳዮች ይፈጽማል፣ ውክልና ይሰጣል፣ በማኅበሩ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል ውል ይዋዋላል፣
2. በማኅበሩ ስም የሚከፈተውን የባንክ ሂሣብ እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሂሣብ ሹሙ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣
3. በጠቅላላው ጉባኤና በቦርድ የሚተላለፉ ውሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣
4. የማኅበሩን የየሶስት ወር እና ዓመታዊ የሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶች እያዘጋጀ (በየሶስት ወሩ እና በየዓመቱ) ለቦርዱ ያቀርባል፣
5. የማኅበሩን ፖሊሲ በማውጣትና የበጀት እና የሥራ እቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣
6. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለማኅበሩ ገቢ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ የማኅበሩን ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ስልቶችን በመቀየስ ያስፈጽማል፣
7. ቦርዱ በሚያወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያሰናብታል፣ ደመወዛቸውንና አበላቸውን ይወስናል፣
8. ከሂሣብ ሹሙ እና ከገንዘብ ያዡ የሥራ ኃላፊነቶች ውጭ ያሉትን የሥራ ድልድሎች በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣
9. ሂሣብ ሹምና ገንዘብ ያዥን ጨምሮ፣ በስሩ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተባበረ፣ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የማኅበሩን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፣
10. የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ ሌሎች የማኔጅመንት ውሣኔዎችን ይሰጣል፣
11. ሥራ አስኪያጁ የማኅበሩ አባል ከሆነ ሐሳቡን ለማጽደቅ ወይም በኃላፊነቱ የተከናወነውን ለማጽደቅ በሚያደርገው ጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ የመስጠት መብት አይኖረውም፣
12. የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔን በማይቃረን ሁኔታ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Charities and Societies

አንቀጽ 22፡ የማኅበሩ ሂሣብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

ሂሣብ ሹሙ ተጠሪነቱ ለማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የማኅበሩን ገቢና ወጪ ሂሣብ ይቆጣጠራል፣ በትክክል እንዲመዘገብና እንዲያዝ ያደርጋል፣
2. የማኅበሩ ሂሣብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሣብ አሠራር ደንብ መሠረት መሆኑን ይቆጣጠራል፣
3. የማኅበሩን የባንክ ሂሣብና ቼክ ወይም ሐዋላ ከሥራ አስኪያጁ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣
4. የማኅበሩ የሂሣብ መዛግብት እና የተለያዩ ሰነዶች በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣
5. የሂሣብ መዝገብ፣ ገቢ እና ወጪ፣ ሀብት እና ዕዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል፣
6. የማኅበሩ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በሚሠማራበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሣብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል።

አንቀጽ 23፡ የማኅበሩ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

ገንዘብ ያዡ ተጠሪነቱ ለማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃፊነቶች ይኖሩታል፤

1. የማኅበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል፣
2. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል፣ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣
3. ለሥራ ማስኬጃና ለማኅበሩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10.000 (አስር ሺህ ብር) ያልበለጠ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፣
4. ከሂሣብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሂሣብ በየወሩ ያመሳክራል፣
5. የማኅበሩን ቼክ ይይዛል፣
6. በጣምራ ፊርማ (በሂሣብ ሹሙ እና በሥራ አስኪያጁ) ሊታዘዝ ወጪ ያደርጋል።

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Agency for Charities and Societies

አንቀጽ 24: የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

1. የማኅበሩ ኦዲተር የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም የቦርድ አባል ሊሆን አይችልም፡፡
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ፤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-
   - 2.1 የማኅበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣
   - 2.2 የማኅበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
   - 2.3 በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላው ጉባኤ ያቀርባል፡፡

አንቀጽ 25: የማኅበሩ የገቢ ምንጭ

የማኅበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

አንቀጽ 26: የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ¼ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል፡፡
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ጸሐፊ ወይም ዳይሬክተር የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ¾ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው፡፡
4. የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ኤጀንሲው ያላጸደቀው እንደሆን ባልጸደቀበት ጉዳይ ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይጠራል፡፡
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በኤጀንሲው በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia The Charities and Societies Agency

አንቀጽ 27፡ ስለ ማኅበሩ መዋሃድና መለወጥ

1. ማህበሩ ወደ ተለያዩ ማኅበራት የሚከፋፈለው፣ ከሌላ ማኅበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ ሌላ አይነት ማኅበርነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ¾ኛ ድምፅ ሲወሰን ነው።

2. ከማህበሩ ጋር የሚዋሃደው ማኅበር ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ፣ ፀሀፊና የማህበሩን ሥራ አስኪያጅ ማካተት ይኖርበታል።

አንቀጽ 28፡ ስለ ማኅበሩ መፍረስ

1. ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ¾ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው።
2. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማህበሩ ሥራ አስኪያጅ የንብረት ዝርዝር (Inventory) አዘጋጅቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ያቀርባል።
3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን ማህበር ወይም የመንግስት አካል ሊያመለክት ይችላል።

አንቀጽ 29፡ የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ከጸደቀበት ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

